M● ST

የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር

# በሳይንስና ቴክኖሎጂ የላቀ የፈጠራ ውጤት ያስመዘገቡ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የሽልማት መመሪያ

566/013

መጋቢት 2008

አዲስ አበባ

# ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ" በሀገር አቀፍ ደረጃ በሳይንስና ቴክኖሎጂ የላቀ የፈጠራ ውጤት ያስመዘገቡ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የሽልማት መመሪያ" ቁጥር 566/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1 "ሽልማት" ማለት በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚማሩ ተማሪዎች በሳይንስ ቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን ላስመዘገቡት የላቀ የፈጠራ ስራ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት፣ ሜዳልያ፣ የገንዘብ እና የስልጠና ማበረታቻ ነው፡፡

2 "የፈጠራ ስራ" ማለት ተማሪዎች በአካባቢ ከሚገኙ ቁሳቁሶች የሚሰሩት የአሰራር ወይም የምርት ናሙና ወይም ሞዴል ነው፡፡

3 "ምርምር" ማለት ከአካባቢዉ ማህበረሰብ እና ከኢንዱስትሪዎች ችግር በመነሳት የተደረገ የመፍትሄ ግኝት ነው፡፡

4 "የሳይንስና ቴክኖሎጂ የትምህርት መስኮች" ማለት የምህንድስና እና የቴክኖሎጂ፣ የተፈጥሮ ሳይንስ፣ የኮምፒዩቴሽናል ሳይንስ፣ የጤና ሳይንስ፣ የግብርና ሳይንስ እና የእንስሳት ህክምና ሳይንስ የትምህርት መስኮች ማለት ነው፡፡

5 "የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት" ማለት አግባብነትና ዕውቅና ያላቸው የመንግስት እና የግል ዩኒቨርሲቲዎችን ማለት ነው፡፡

6. "ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፡፡

7. "ሀገር አቀፍ የሽልማት ገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ" ማለት በሀገር አቀፍ ደረጃ የተወዳዳሪ ተማሪዎች የፈጠራና የምርምር ውጤት ግምገማና መረጣን በበላይነት የሚያካሄድ አካል ነው፡፡

8. በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀ አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

### 3. ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች፣ የማህበረሰቡንና የኢንዱስትሪን ችግር መፍታት የሚችሉ ምርምሮችንና የፈጠራ ስራዎችን እንዲሰሩ ለማበረታታትና ዕውቅና ለመስጠት ነው፡፡



በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Science and Technology

4 **የመመሪያው ተፈፃሚነት**

ይህ መመሪያ በሁሉም የመንግስት እና የግል የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በመደበኛ ትምህርት መርሀ ግብር በመማር ላይ ያሉ እና የፈጠራና ምርምር ስራቸውን ለውድድር በሚያቀርቡ ኢትዮጵያዊያን የመጀመሪያ ዲግሪ ተማሪዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የሽልማት ምድቦች፣ ተወዳዳሪዎች ሚሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች እና መምረጫ መስፈርቶች

5 **የሽልማት ምድቦች**

በሳይንስ እና ቴክኖሎጂ የትምህርት መስኮች የፈጠራ ስራን ለማበረታታት ለተማሪዎች የሚሰጠው ሽልማት ከዚህ በታች የተመለከቱት ሁለት የሽልማት ምድቦች ይኖሩታል፡፡

1. የመጀመሪያ ዲግሪ ተማሪዎች የሽልማት ምድብ እና
2. የመጀመሪያ ዲግሪ የሴት ተማሪዎች ሽልማት ምድብ ናቸው፡፡

6 **ተወዳዳሪዎች ማሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች**

1. በዚህ መመሪያ መሰረት ለሽልማት የሚቀርቡ እጩ ተወዳዳሪዎች በመደበኛ የትምህርት መርሀ-ግብር የሳይንስና ቴክኖሎጂ ትምህርት የሚማሩ ኢትዮጵያዊያን ተማሪዎች መሆን ይኖርባቸዋል፣
2. ተወዳዳሪዎች የተሟላና በተቋሙ ከፍተኛ ኃላፊ የተፈረመበት የማመልከቻ ቅፅ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፣
3. ለውድድር የሚቀርቡ የዕጩ ተወዳዳሪዎች የፈጠራ ሞዴሎች እና ናሙናዎች በተወዳዳሪው ግለሰብ ብቻ የተሰሩ ስለመሆናቸው ከሚማሩበት ተቋም ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችሉ መሆን አለባቸው፣
4. ለውድድር የሚቀርቡ ስራዎች መረጃ በሰነድ፣ በፎቶ ፣ በተንቀሳቃሽ ምስል ወይም በሌላ አስፈላጊ በሆኑ የማቅረቢያ ዘዴዎች የተደገፉ መሆን ይኖርባቸዋል፣
5. ከአንድ የትምህርት ተቋም የሚቀርቡ እጩ ተወዳዳሪዎች በተመሳሳይ ስራ ለውድድር መቅረብ አይችሉም፣
6. ለሀገር አቀፍ ሽልማት ውድድር የሚላኩ ዕጩ ተወዳዳሪዎች በሰሩት የላቀ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምርና የፈጠራ ስራ በዩኒቨርሲቲው ደረጃ ተወዳድረው የተመረጡ ወይም የተሻሉ እና የተሻሉ ስለመሆናቸው ማስረጃ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 7. የመምረጫ መስፈርቶች

1. የእጩ ተወዳዳሪ ተማሪዎች ሥራዎች ዝርዝር ከዚህ መመሪያ ጋር የተያያዘው አባሪ በሚጠይቀው መሰረት መፃፍ ይኖርባቸዋል፣
2. ከላይ በተራ ቁጥር 1 ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በመስፈርቶቹ የተሠሩ ሥራዎች በዝርዝር ካልተገለጹ ለመስፈርቱ የተሠጠውን ነጥብ አያገኙም፣
3. ለእያንዳንዱ የሽልማት ምድብ የመምረጫ መስፈርቶች ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው አባሪ 1 መሰረት ይሆናል፡፡

# ክፍል ሶስት

# <u>የተሸላሚዎች ድልድልና ብዛት፣ የሽልማቱ አይነት፣ የሽልማት አስተዳደርና የክትትል ስርዓት</u>

## 8. የተሸላሚዎች ድልድልና ብዛት

1. በየዓመቱ በየሽልማት ምድቡ ለውድድር የሚቀርቡ ተማሪዎች ብዛት ከዩኒቨርሲቲዎች የቅበላ አቅም አንፃር ሲሆን ዝርዝሩ በሚኒስቴሩ የሚገለጽ ይሆናል፣
2. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሴት ተማሪዎችን ለማበረታታት እና በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ተሳትፏቸውን ለማሳደግ ከወንዶች ጋር እኩል ተወዳድረው ያልተመረጡ ሴት ተማሪዎች በአንቀጽ 5(2) መሰረት ለብቻቸው በማወዳደር እጩዎቻቸው ተመርጠው የሚላኩ ይሆናል፣
3. በአንቀጽ 5 የተመለከቱት ምድቦች በአንድ ዓይነት የመምረጫ መስፈርቶች ይከናወናሉ፡፡

## 9. የሽልማቱ ዓይነት

### አሸናፊ ተማሪዎች፡-

1. የዕውቅና የምስክር ወረቀት፣
2. ሜዳሊያ፣
3. የገንዘብ ማበረታቻዎች ያገኛሉ፣
4. ከተሸላሚ የፈጠራ እና የምርምር ስራዎች መካከል በመምረጥ ሀገር አቀፍ ደረጃ በሚዘጋጁ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ኤግዚቢሽኖች ለህብረተሰቡ እንዲቀርቡ ይደረጋል፣

5. ከተሸላሚዎች መካከል በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር የአጭር ጊዜ የአቅም ማጎልበቻ ስልጠናዎች የሚያገኙበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

## 10. የሽልማት አስተዳደርና የክትትል ስርዓት

1. ሽልማቱን የሚያስተዳድሩትና አፈፃፀሙን የሚከታተሉት የሚመለከታቸው የፌደራል ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ሲሆኑ እነሱም ሚኒስቴሩ፣ የትምህርት ሚኒስቴርና የሴቶችና ሕፃናት ጉዳይ ሚኒስቴር ናቸው፣

# ክፍል አራት

# የሽልማት ገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ

## 11. ሀገር አቀፍ የሽልማት ገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ ስለማቋቋም

በሀገር አቀፍ ደረጃ የተወዳዳሪዎችን የፈጠራና ምርምር ስራ ግምገማና መረጣ በበላይነት የሚያስፈጽም ሀገር አቀፍ የሽልማት ገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ ይቋቋማል፡፡

### የኮሚቴው አባላት

1. ሚኒስቴሩ ---- ሰብሳቢ
2. ትምህርት ሚኒስቴር....... አባል
3. የሴቶችና ሕፃናት ጉዳይ ሚኒስቴር....... አባል
4. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተወካይ....... አባል
5. ከሙያው ጋር ተያያዥነት ካላቸው አጋር ተቋማትና የሳይንስና ቴክኖሎጂ የሙያ ማኅበራት ወይም ከህዝብ ክንፍ የሚወከሉ አባላት ይኖሩታል፡፡

## 12. የዩኒቨርሲቲዎች የገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ ስለማቋቋም

ዩኒቨርሲቲዎች በተቋም ደረጃ የተወዳዳሪዎችን የፈጠራና ምርምር ስራ ግምገማና መረጣ የሚያስፈጽም ገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ በራሳቸው ያቋቁማሉ፡፡

# ክፍል አምስት

# ተግባር እና ሀላፊነት

## 13. የሚኒስቴሩ ተግባር እና ሀላፊነት

ሚኒስቴሩ፡-

1. በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሚደረገው ሽልማት በጀት ያስመድባል፣
2. ጉዳዩ የሚመለከታቸው የፌዴራል መ/ቤቶችን ያስተባብራል፣

3. በየደረጃው የሚካሄደውን የሽልማት አፈጻጸም ክትትል ያደርጋል፡
4. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ዕጩ ተወዳዳሪዎችን መርጠው እንዲልኩ የሀገር አቀፍ ሽልማት ፕሮግራምና የሚልኩትን የተወዳዳሪ ብዛት በደብዳቤ ይገልፃል፣
5. በየሽልማት ምድቡ የሚቀርቡ የተወዳዳሪዎችን መረጃ በማደራጀት የመጀመሪያ መረጣ በማድረግ ለሀገር አቀፍ ገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ ለቀጣይ ግምገማ ዝግጁ ያደርጋል፡
6. የተሸላሚዎችን መረጃ ያደራጃል፡
7. የላቀ ውጤት ላስመዘገቡት የምርጦች ምርጥ ተሸላሚዎች የማበረታቻ ሽልማት ይሰጣል፡
8. ውጤታማ የሆኑ ፈጠራዎችንና ምርምሮችን ለህብረተሰቡ ተደራሽ እንዲሆኑ ያደርጋል፡
9. ለተሸላሚዎችም የስራ ፈጠራና የአቅም ግንባታ የአጭር ጊዜ ስልጠና እና የገበያ ትስስር የሚፈጠርበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

## 14. ዩኒቨርሲቲዎች ተግባር እና ሀላፊነት

### ዩኒቨርስቲዎች፡-

1. በያንዳንዱ እርከን ማለትም በትምህርት ክፍል ወይም በፋካልቲ የሚደረገውን የአመራረጥ ሂደት ይከታተላሉ፣ እንዲሁም ለውድድር የቀረቡ የተወዳዳሪዎች የፈጠራና ምርምር ውጤት በትክክል መሬት ላይ ያሉ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ፣
2. ለሀገር አቀፍ ሽልማት ዕጩ ተወዳዳሪዎችን መርጠው ከመላካቸው በፊት በራሳቸው በጀት ብቁ ተማሪዎችን አወዳድረው እንዲሸልሙ ይበረታታሉ፣
3. ዩኒቨርሲቲዎች የላቀ ውጤት ያስመዘገቡ እጩ ተወዳዳሪዎችን ስም ዝርዝር፣ የኮሚቴውን ቃለጉባኤ፣ ዕጩዎች በየመስፈርቱ የሰሯቸውን ሥራዎችና ማስረጃዎች በማያያዝ ዝርዝሩን በማጠቃለያ አባሪ ቅጽ ሞልተው ለሀገር አቀፍ የምርጦች ምርጥ ውድድር ለሚኒስቴሩ ይልካሉ፡፡

## 15. ሀገር አቀፍ የሽልማት ገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ ተግባር እና ሀላፊነት

### ኮሚቴው፡-

1. በሁሉም የሽልማት ምድቦች የቀረቡ ተወዳዳሪዎችን ሰነድ እና ውጤት ትክክለኛነት ያረጋግጣል፡

2. በተወዳዳሪዎች የቀረቡ የፈጠራና የምርምር ፕሮጀክቶችን በጥልቀት በማየት በተሰጠው መስፈርት ይገመግማል፣ የማለፊያ ነጥብ በማስቀመጥ ለሽልማት ብቁ የሆኑትን በደረጃ ለይተው ያቀርባል፡
3. በተወዳዳሪዎች የተሰሩ ስራዎችን በመስፈርቶቹ መሰረት በመገምገም በሀገር አቀፍ ደረጃ ውጤት ይሰጣል፡
4. የተመረጡትን እጩ ተሸላሚዎችን ጠቅላላ የአመራረጥ ሂደትና ውጤት ሪፓርት ለሚኒስቴሩ የበላይ አመራር በማቅረብ ያፀድቃል፡፡

## 16. የዩኒቨርሲቲዎች የግምገማና መራጭ ኮሚቴ ተግባር እና ሀላፊነት

ኮሚቴው፡-

1. ተማሪዎች ለውድድር እንዲቀርቡ ጥሪ ያደርጋል፡
2. የቀረቡ ተወዳዳሪዎችን ሰነድ ትክክለኛነት ያረጋግጣል፡
3. በተወዳዳሪዎች የቀረቡ የፈጠራና የምርምር ፕሮጀክቶችን በጥልቀት በማየት በተሰጠው መስፈርት ይገመግማል፣ ብቁ የሆኑትን በደረጃ ለይተው ለዩኒቨርሲቲው በቃለ ጉባኤ ያቀርባል፡
4. ሁለት ዕጩ ተወዳዳሪዎች ተመሳሳይ ውጤት ካገኙ ተጨማሪ የመመዘኛ መስፈርቶችን በማውጣት እንዲለዩ ያደርጋል፡፡

# ክፍል ስድስት

## <u>የተሸላሚዎች አመራረጥ ሂደት፣ የቅሬታ አፈታት ስርዓት፣ ክትትልና ግምገማ</u>

## 17. የተሸላሚዎች አመራረጥ ሂደት

1. ሁሉም እጩዎች የሚመረጡት በአብዛኛው የሳይንስና ቴክኖሎጂ ትምህርትን መሰረት በማድረግ በሰሩት የፈጠራና ምርምር ስራ ሞዴሎች/ናሙናዎች ሲሆን እንደ አግባብነቱ ሌሎች ደጋፊ መመዘኛዎችም ታሳቢ ይደረጋል፣
2. የእጩ ተሸላሚ መረጣ የሚጀመረው በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ከሚገኙ ትምህርት ክፍሎች ይሆናል፡
3. ሁለት ዕጩ ተወዳዳሪዎች ተመሳሳይ ውጤት ካገኙ ተቋሙ ተጨማሪ የመመዘኛ መስፈርቶችን በማውጣት እንዲለዩ ያደርጋል፡
4. የሀገር አቀፍ ገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ በተቀመጡት መስፈርቶች መሰረት ዕጩ የምርጦች ምርጥ ተሸላሚዎችን በመምረጥ ለሚኒስቴር ~~መስሪያ~~ ቤቱ የበላይ አመራር በማቅረብ ያፀድቃል፡

5. የፀደቁ የምርምርና የፈጠራ ውጤቶች በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች ለሚመለከታቸው አካላት ተደራሽ ይደረጋሉ፡፡

## 18. የቅሬታ አፈታት ስርዓት

ተወዳዳሪዎች ወይም ተሸላሚዎች ወይም ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት በሀገር አቀፍ ሽልማት አመራረጥ ሂደት፣ የተለያዩ አገልግሎቶች እና አሰራሮች ላይ ቅሬታ ካላቸው በሚኒስቴሩ የቅሬታ አቀራረብ አፈታት ስነ-ስርዓት መሰረት የሚፈታ ይሆናል፡፡

## 19. ክትትልና ግምገማ

በየደረጃው ያሉ የሽልማት አስፈፃሚ አካላት የሽልማቱን አፈፃፀም በየጊዜው ይከታተላሉ፣ ይገመግማሉ እንዲሁም የተወዳዳሪዎችን መረጃ በመረጃ ቋት ይይዛሉ፡፡

# ክፍል ሰባት
# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 20. መመሪያውን ስለማሻሻል

ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው መመሪያውን ሊያሻሽል ይችላል፡፡

## 21. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በሚኒስትሩ ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

መጋቢት 30. ቀን 2008 ዓ.ም

አብይ አህመድ

ሚኒስቴር

አብይ አህመድ
ሚኒስትር

## አባሪ 1 የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ተወዳዳሪ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የመምረጫ መስፈርቶች (ለመጀመሪያ ዲግሪ ተማሪዎች ብቻ)

| ተ.ቁ | መስፈርቶች | የሚሰጠው ነጥብ መጠን | በተቋሙ የተሰጠው ውጤት | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ተማሪው በአትራቢያው ከሚገኝ ማህበረሰብ ወይም ከኢንዱስትሪ ችግር በመነሳት የሰራቸው የምርምርና የፈጠራ ስራዎች ናሙና ጥንካሬ | 50 | | የምርምርና የፈጠራ ስራዎቹ በትክክል በተወዳዳሪው የተሰራ ስለመሆኑ በዲፓርትመንት የተረጋገጠ መሆን አለበት፡፡ |
| | • የማህበረሰቡንና የኢንዱስትሪውን ችግር የፈታ ስለመሆኑ | 25 | | |
| | • በተወዳዳሪው የተሰሩ የፈጠራና የምርምር ስራዎች ውስብስብነት | 15 | | |
| | • በቀላሉ ወደ ምርት የሚቀየሩበት | 10 | | |
| 2 | የፈጠራ ሥራዎቹ ወቅታዊ ፋይዳ | 10 | | የፈጠራ ሥራዉ ወቅታዊ የሆነ የማህበረሰቡን ችግር ላይ ያተኮረ ሆኖ ቅድሚያ ትኩረት በተሰጣቸው ዘርፎች መሆኑ፡፡ |
| | • ከፍተኛ | 10 | | |
| | • መካከለኛ | 7 | | |
| | • ዝቅተኛ | 4 | | |
| 3 | የተማሪው የመጨረሻዎቹ ሁለት ተከታታይ ሴሚስተር የሳይንስና ቴክኖሎጂ ትምህርቶች አማካኝ ውጤት | 10 | | ተማሪው በተግባርና በንድፈ ሀሳብ ፈተናዎች ያመጣው ነጥብ በAverage/ በአማካኝ ተሰልቶ እንደልዩነቱ ነጥብ ይሰጣል፡፡ |
| 4 | ተማሪው ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ያለው የስራ መስተጋብር (ቲም ወርክ)፣ በቢተ ሙከራና ወርክሾፖች ውስጥ የማዘውተር ልምድ | 10 | | |
| | • ከፍተኛ | 10 | | |

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር · The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Science and Technology

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | • መካከለኛ | 7 | | |
| | • ዝቅተኛ | 2 | | |
| 5 | በዩኒቨርሲቲው ተማሪው ከመመረቂያ ፅሁፍ ውጪ ያዘጋጃቸው የምርምር ፅሁፎች | 10 | | |
| | • የምርምር ስራው መነሻ ሀሳብ አስፈላጊነት | 3 | | |
| | • ለወደፊት ምርምር ለሚሰሩ ተማሪዎች እና ለምርታማነት ያለው አስተዋፅኦ | 3 | | |
| | • የምርምር ስራውን ተግባራዊ ለማድረግ ያለው አመችነት | 2 | | |
| | • አዲስነት (originality) | 2 | | |
| 6 | በሙያ ማህበራት፣ በካምፓስ እንቅስቃሴዎች እና ማህበረሰብ አገልግሎት ላይ ያለው ንቁ ተሳትፎ | 5 | | |
| | • በሳይንስና ቴክኖሎጂ የሙያ ማህበራት በመታቀፍ ያበረከታቸው አስተዋፅኦዎች | 2 | | |
| | • የአካባቢውን ማህበረሰብ ለማገልገል በሚደረጉ ጥረቶች ያለው ቀጥተኛ ተሳትፎ | 3 | | |
| 7 | ተማሪው በትምህርት ቤቱ ያለው ስነ ምግባር | 5 | | ተማሪው ከደባል ሱስ ነፃ መሆኑ፣የትምህርት ሰዓቱን በአግባቡ የሚጠቀም መሆኑ ለመምህራንና ለዩኒቨርሲቲው ሰራተኞች ያለው ከበሬታ በዲፓርትመንት ወይም Academic Council የተረጋገጠ መሆን አለበት፡፡ |
| | • እጅግ በጣም ጥሩ | 5 | | |
| | • በጣም ጥሩ | 4 | | |
| | • ጥሩ | 2 | | |